Bundesamt
für Migration
und Flüchtlinge

Bundesministerium
des Innern

# ስለኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ (eAT) ሊኖርዎት የሚገባ ግንዛቤ



www.bamf.de/eaufenthaltstitel

# ማውጫ


1 የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ 5

2 ፎቶ እና የጣት አሻራ 7

3 ልዩ፤ልዩ ተጨማሪ ድንጋጌዎች (ልዩ ሁኔታዎች) 9

4 በኦንላይን የማንነት የማረጋገጥ ተግባር 10

5 የኤሌክትሮኒክ ፊርማ 13

6 የመኖሪያ ፈቃድ ሊያሰጥዎ የሚያስችሉ አዳዲስ ጠቃሚ አገልግሎቶች 15

7 ስለመረጃ አያያዝ 16

8 የመኖሪያ ፈቃድ ካርድዎ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ስለሚያጋጥምዎት ችግር 17

9 ሌሎች ችግሮች ቢፈጠሩስ? 18

10 የእኛ መሠሪያ ቤት ችግሩን ለመፍታት ምን ጊዜም ዝግጁ ነው! 19

# መግቢያ

እስከ አሁን ድረስ የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት/Ausländerbehörde ሲሰጥ የነበረው (የመኖሪያ ፈቃድ Aufenthaltserlaubnis፣ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ/Niederlassungserlaubnis፣ ቋሚ የአውሮፓ ህብረት መኖሪያ ፈቃድ ወይም ሰማያዊ የአውሮፓ ህብረት ካርድ/Daueraufenthalt-EG እና Blaue Karte EU) ሆኖ መታወቂያና ፓስፖርት አንድ ላይ መለጠፍ በሚያስችል መልኩ የተዘጋጀ ነበር።

እ.አ.አ. ከሴፕቴምበር 1 ቀን 2011 ጀምሮ የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ (eAT) የተለያዩ የኤሌክትርኒክ ተግባራት በማካተት Aufenthaltserlaubnis ራሱን ችሎ ክሬዲት ካርድ በሚመስል መልክ ተዘጋጅቶ ይሰጣል። ይህ ካርድ ለሁሉም የሶስተኛ ሀገር ዜጎች ማለትም (የአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ዜጎች ላልሆኑ) የሚሰጥ ነው።

ለአውሮፓ ህብረት ዜጎች እንዲሁም ለስዊዝ ዜጎችና ለቤተሰብ አባሎቻቸው ሲሰጥ የነበረው የመኖሪያ ፈቃድ እስካሁን ድረስ (የመኖሪያ ፈቃድ ካርድ/Aufenthaltskarte፣ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ካርድ/Daueraufenthaltskarte ወይም የስዊዝ ዜጎች የመኖሪያ ፈቃድ) በዶኩመንት መልክ የተዘጋጀ ነበር። አዲሱ የመታወቂያ ካርድ እነዚህን ሁሉ የመኖሪያ ፈቃድ ዓይነቶች ያጠቃለለ ነው።

በeAT የመታወቂያ ካርድ ውስጥ ያለው ችፕ የግለሰብ መረጃዎችን፣ ማለትም የባዮሜትሪክ ባህሪያት ያላቸውን (ፎቶዎች፣ ዕድሜያቸው 6 እና ከዚያ በላይ ከሆኑ ግለሰቦች ደግሞ ሁለት የጣት አሻራዎች) እና እንዲሁም ማንኛውንም ተጨማሪ መረጃዎች ያካተተ ነው። በተጨማሪም መረጃ የሚሸከመው ችፕ የኤሌክትሮኒክ ማንነት ማረጋገጫ ያለው ሲሆን የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ለማስቀመጥ እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

## ስለ ኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ የሚታወቁ መረጃዎች

- እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 1 ቀን 2011 ጀምሮ ተግባራዊ መሆኑ፣
- በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያለውን ምልክት የተለጠፈበትን መታወቂያ መተካቱ፣
- ለሶስተኛ ሀገራት ዜጎች (የአውሮፓ ህብረት ሀገራት ዜጎች ላልሆኑ) በአውሮፓ ህብረት አባል ሀገራት ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የመኖሪያ ፈቃድ አሰጣጥ ሥራ ላይ መዋሉ፣
- በክሬዲት ካርድ መልክ የተዘጋጀ መሆኑ፣
- ብዙ መረጃ መያዝ የሚችል ችፕ የተገጠመለት መሆኑ፣
- የማጭበርበር ወንጀልን ለመከላከል እንዲቻል፣ ዕድሜው 6 እና ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ግለሰብ የሚሰጠው የመኖሪያ ፈቃድ በዲጂታል ፎቶና በጣት አሻራ ላይ የተ መሠረተ እንደመሆኑ በመኖሪያ ፈቃድና መታወቂያዉን የያዘው ግለሰብ ማንነት በማያሻማና ግልጽ በሆነ ሁኔታ ማመሳከር ማስቻሉ፣
- 
- በኤሌክትሮኒክ ማንነት የማረጋገጫ ዘዴ በመታገዝ በኢንተርኔትና በተለያዩ መሳሪያዎች በመታገዝ የንግድና ሌሎችንም ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል መሆኑ፣
- የዲጂታል ሰነዶች ሕጋዊ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ኤሌክትሮኒክ ፊርማ እንዲሰፍርባቸው ማስቻሉ የሚሉት ናቸው።

# 1 የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ




## የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ eAT ለምን አስፈለገ?

በአውሮፓ ህብረት ካውንስል ድንጋጌ ቁጥሮች 1030/2002 እና 380/2008 መሠረት ሁሉም የህብረቱ አባል ሀገራት የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ ተግባራዊ ያደርጋሉ። ዓላማውም በሁሉም አባል ሀገራት ለሶስተኛ ሀገር ዜጎች የሚሰጡ የመኖሪያ ፈቃዶች ወጥነት ያላቸው እንዲሆኑ በማሰብ ነው። ይህ አሠራር በባዮሜትሪክ መረጃ አማካይነት የመታወቂያ ካርዱና የያዥው ባለቤት ማንነት ትክክለኝነ ት የማያሻማና ግልጽ እንዲሆን በማስቻል የማጭበርበር ድርጊቶችን ለመቆጣጠር ታስቦ ነው።

## እስከ አሁን  በሥራ ላይ ያሉት የመኖሪያ ፈቃዶች የመጠቀሚያ ጊዜያቸው መቼ ያበቃል?

አገልግሎት እየሰጡ ያሉት የመኖሪያ ፈቃዶች ማለትም ፓስፖርቶችና ተተኪ የጉዞ ዶኩመንቶች የማብቂያ ጊዜያቸው በላያቸው ላይ እስከተጠቀሰው የጊዜ ገደብ አግልግሎት መስጠት የሚችሉ ሲሆን ይህም ግፋ ቢል እስከ እ.አ.አ 30.04.2021 ድረስ ይሆናል።

## የኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ eAT የአገልግሎት ጊዜው ምን ያህል ነው?

የeAT የአገልግሎት ዘመን፣ የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት የተሰጠውን ስልጣንና ኃላፊነት ተመርኩዞ በሚያወጣው ደንብ መሠረት በሚሰጠው የመኖሪያ ፈቃድ ዓይነት መሠረት የሚወሰን ይሆናል። የጊዜ ገደብ የሌለው የመኖሪያ ፈቃድ የተሰጠ እንደሆነ የካርዱ አገልግሎት ለአስር ዓመት ይሆንና ከእዚያ በኋላ ሌላ የሚታደስ የመታወቂያ ካርድ ይሰጣል።

**!**

ልብ ይበሉ፣

እስካሁን ሲሠራበት የነበረው የመኖሪያ ፈቃድ ዝርዝር መሥፈርት/ገለጻ እንደሚጠይቀው ሁሉ፣ በዚህኛዉም በeAT አገልግሎት ማግኘት የሚቻለው ግለሰቡ የአገልግሎት ግዜው ያላለፈ ፓስፖርት ወይም አማራጭ የጉዞ ዶኩመንት ሲያቀርብ ብቻ ይሆናል። eAT ከፓስፖርቱ ወይም ከአማራጭ የጉዞ ዶኩመንቱ ጋር አግባብነትና ተያያዥነት ያለው መሆን ይኖርበታል። ስለእዚህ የያዙት ፓስፖርት ወይም ሌላ የጉዞ ዶኩመንት ጊዜው ሳያልፍበት ማሳደስ ይኖርብዎታል።

## የኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ የeAT ተግባራት በዝርዝር

ካለአግባብ መጠቀም እንዳይቻል ለመከላከል የእርስዎ ፎቶ እና የጣት አሻራ በeAT ችፕ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል። እንደዚሁም በባዮሜትሪክ አማካይነት የእርስዎ የግል የማንነት መለያ መረጃዎች ተገቢ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

> **ልብ ይበሉ፣**
> የእርስዎን ፎቶ እና የጣት አሻራዎች ማየት ወይንም መመርመር የሚችሉት የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ማለትም ፖሊስና የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት (Ausländerbehörde) ብቻ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች የተከማቹበት ችፕ ያለበት የካርድ ክፍል ልዩ ጥበቃ እንዲኖረው ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

የኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ eAT ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ፣ ከነባሩ የመኖሪያ ፈቃድ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ተጨማሪ ድንጋጌዎችና የሌሎች ልዩ ሁኔታዎች ገለጻ የተደረገበት ምልክት ታትሞ በፓስፖርቱ ላይ እንደቀድሞው አይለጠፍበትም። በዚህ ምትክ መረጃዎቹ በችፑ ውስጥ እንዲከማቹ ከተደረገ በኋላ እንደገና ራሱን ችሎ በአባሪ ቅፅ ላይ ይታተማል። ይህ አባሪ ቅፅ ከeAT ጋር አብሮ ይሰጥዎታል።

> **ልብ ይበሉ፣**
> በችፕ ዉስጥ ተከማችተው የሚገኙትን መረጃዎች መጠቀም የሚችሉት የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት፣ ማለትም ፖሊስና የጉምሩክ ባለስልጣናት ብቻ ይሆናሉ።

የመታወቂያ ካርዱ ከሚሰጠው አገልግሎት አንዱና አዲስ „በኦንላይን ማንነትን ማረጋገጥ" ማስቻል ነው። ይህም በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ስልት በመባል ይታወቃል። ይህ አሠራር በeAT አማካይነት በድረ-ገፆች ወይም በሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ላይ ያለምንም ስጋት መመዝገብና አስተማማኝ በሆነ መንገድ ማንነትዎን ማረጋገጥ ያስችልዎታል። በኢንተርኔት አማካይነት ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ሲፈጥሩ የተገናኙት በእውነትም ከዚያ የሚፈልጉት ግለሰብ ጋር መሆኑን በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴ እርግጠኛ መሆን ይችላሉ። ይህ የማረጋገጫ ስልት ለግል መረጃዎችዎ አስተማማኝ የጥበቃ ከለላ ይሰጣል።

> **ልብ ይበሉ፣**
> የትኛው የግል መረጃዎ ለሌላ ሊተላለፍ እንደሚችል የትኛው እንደማይቻል ወሳኙ ራስዎ ነዎት።

አዲሱ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ እንደማንኛዉም የእጅ ፊርማ ሕጋዊ ተፈጻሚነት አለው። ይህ ፊርማ ቀላልና ምቹ ከመሆኑም በላይ ኦንላይን በሚደረጉ ስምምነቶችና ማመልከቻዎች ላይ እንደሰፈረ እንደ ማንኛዉም የእጅ ፊርማ በሕግ ተፈጻሚነት አለው። ስለሆነም በኮምፒውተር በመጻፍ፣ በወረቀት አትሞና የእጅ ፊርማ አስፍሮ በፖስታ መላክ አላስፈላጊ ይሆናል።

## በኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ (eAT) ውስጥ በሚገኘው ችፕ ምን ዓይነት መረጃዎች ይገኛሉ?

በመታወቂያ ካርዱ ላይ ታትመው የሚገኙት መረጃዎች (ለምሳሌ ስም፣ የወላጅ ስም፣ አድራሻ ወ.ዘ.ተ) ሲሆኑ እነዚሁ መረጃዎች ችፑ ውስጥ በዲጂታል መልክ ተቀምጠዋል። በተጨማሪም በችፑ ውስጥ የባዮሜትሪክ ዳታ (የጣት አሻራዎችና ፎቶ) እንዲሁም ማናቸውም ተጨማሪ ድንጋጌዎች (ልዩ ሁኔታዎች) ሰፍረው ይገኛሉ።

# 2 ፎቶና የጣት አሻራ




ፎቶው በኤሌክትሮኒክ መልክ በችፑ ውስጥ የተቀመጠ ሲሆን በመታወቂያው ካርድ ላይም ታትሞ ይገኛል። ፎቶው ቀጥለው የተዘረዘሩትን መሥፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

- ወቅታዊ መሆን አለበት።
- የፊትዎ ሙሉ ገጽ ፊት ለፊት መታየት አለበት፤ ፊትዎ ሙሉ ለሙሉ እንዲታይ መሸፈን የለበትም በጎን በኩል የተነሳ መሆን የለበትም።
- በእምነት ላይ የተመሠረተ የራስ ሽፋን የፊት ገፅታን የማይከልል እስከሆነ ድረስ ይፈቀዳል።
- ዓይኖች የተከፈቱና በግልፅ የሚታዩ መሆን አለባቸው።
- ለየት ያለ ምክንያት ካጋጠመ ለምሳሌ የህክምና/ህመም ሁኔታ ካለ በልዩ ሁኔታነት ታይቶ ሊፈቀድ ይችል ይሆናል።

! ፎቶግራፍዎን አስመልክቶ መሟላት ስለአለባቸው መሥፈርቶች ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገዎት የሚከተለውን ድረ-ገፅ ይጎብኙ። www.bmi.bund.de

የአውሮፓ ህብረት አባል ካልሆነ ሀገር የሚመጣ ማንኛውም የውጭ ዜጋ ዕድሜው 6 እና ከዚያ በላይ ከሆነ በመታወቂያ ካርዱ ችፕ ውስጥ የሁለት ጣቶች አሻራዎች እንዲካተቱ ይደረጋል። በእዚህም መንገድ በመታወቂያ ካርዱና በባለቤቱ ማንነት መካከል በማያሻማና ግልጽ በሆነ መንገድ ለማመሳከር በማስቻል ከማጭበርበር ድርጊቶች ለመከላከል ያገለግላል።



## የጣት አሻራዎች ከeAT ውጭ በቋሚነት እንዲከማቹ ይደረጋል?

በውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት የጣት አሻራዎችዎ በመረጃነት ተከማችተው የሚቀመጡት የeAT ካርድዎን እስከሚቀበሉበት ጊዜ ድረስ ብቻ ይሆናል፡፡ ከእዚያ በኂላ ባለስልጣኑ የጣት አሻራ መረጃዎችዎን በዘላቂነት እንዲሰረዙ ያደረጋል፡፡ የeAT ካርድ የሚያትመው የፌዴራል ማተሚያ መ/ቤትም ቢሆን የእርስዎን መረጃዎች አያከማችም፡፡ ሀገር ዓቀፍ የመረጃ ማዕከል ለማቋቋም የሚያስችል የአዋጅ ሕግ የለም፡፡

## በኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ eAT ችፕ ውስጥ የሚገኘውን ፎቶ እንዲሁም የጣት አሻራዎች ማየትና ማጣራት የሚችለው አካል ማን ነው?

የመኖሪያ ፈቃዱን ሕጋዊነትና የባለቤቱን ማንነት ማጣራት ይቻላቸው ዘንድ ፎቶውንም ሆነ የጣት አሻራዎቹን ማየት የሚፈቀድላቸው አግባብ ያላቸው ህጋዊ ባለስልጣናት ማለትም ፖሊስና የውጭ ዜጎች ጉዳይ መ/ቤት ባለስልጣናት ብቻ ናቸው፡፡ ለእዚህም የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ (eAT) ለሚመለከተው ባለስልጣን መቅረብ ይኖርበታ፡፡ ይህን መረጃ በኦንላይን ማንበብ አይቻልም፡፡

ማናቸውም ከቦታ ቦታ የሚተላለፉ መረጃዎችም ሆኑ eAT ዓለም አቀፋዊ መስፈርት ባሟሉ የኤሌክትሮኒክ የመረጃ ኮዶች የተጠበቁ ናቸው፡፡ በeAT ተከማችቶ የሚገኘውን መረጃ ማን ምን ሊያይ እንደሚፈቀድለት በባለሥልጣን መ/ቤት መመሪያ የተወሰነ ነው፡፡

## የጣት አሻራዎች የሚወሰዱት እንዴት ነው?

የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ለውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት የሚያመለክት ማን ኛውም ሰው የጣት አሻራው ይወሰዳል፡፡ አሻራው የሚወሰደው ምንም ዓይነት ቀለም በማያስፈልገው የስካን ማድረጊያ መሣሪያ  ይሆናል፡፡ አብዛኛውን ግዜ የሁለት ጣቶች አሻራ ከእያንዳንዳቸው ሶስት ጊዜ ይወሰዳል፡፡ ከተወሰዱት አሻራዎች መካከል የተሻሉት ተመርጠው ሥራ ላይ ይውላሉ፡፡

## ከየትኛዎቹ ጣቶች ላይ ነው አሻራ የሚወሰደው?

በመሠረቱ ከሁለቱ እጆች አመልካች ጣቶች ለeAT አገልግሎት አሻራ ሊወሰድ ይችላል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ከትንሿ ጣት በስተቀር ከሌሎቹ ጣቶች አሻራዎች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡

# 3 ተጨማሪ ድንጋጌዎች (ልዩ ሁኔታዎች)




ተጨማሪ ድንጋጌዎች (ልዩ ሁኔታዎች) ከመኖሪያ ፈቃዱ ጋር አብሮ ተሰጥቶ ከሆነ በችፑ ውስጥ መረጃዎቹ እንዲከማቹ ይደረጋል። እንደገናም በአባሪ ቅፅ ላይ እንዲታተሙ ተደርጎ በመታወቂያ ካርዱ ላይ አባሪ ቅፁን ይመለከቱ „siehe Zusatzblatt“ የሚል ማመላከቻ ይለጠፍበታል። በተጨማሪም በድንጋጌዎች (ልዩ ሁኔታዎች) ላይ ለውጥ ከተደረገ እንደገና አዲስ አባሪ ቅፅ ታትሞ ይሰጣል። ቺፑ ውስጥ ያሉትም መረጃዎች አስፈላጊው ለውጥ ይደረግባቸዋል። ይህም ሲደረግ በለዉጡ ምክንያት አዲስ eAT ካርድ ማውጣት አስፈላጊ አይሆንም።

**!**

ልብ ይበሉ፧
እነዚህን ተጨማሪ ድንጋጌዎች ለማየት ወይንም ለመቆጣጠር የሚችሉት የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ማለትም የፖሊስና የጉምሩክ ባለስልጣናት ብቻ ናቸው።
ይህን ለማድረግ eAT ካርድ ለሚመለከተው ባለስልጣን መቅረብ ይኖርበታል።
መረጃውን በኦንላይን ማየትና ማንበብ አይቻልም።

# 4 ኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ተግባር

## ኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት ምንድን ነው ?

የኦንላይን ማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት በሚሰጥበት ቦታ ሁሉ በኢንተርኔትም ሆነ ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጭ መሳሪያዎች ባለስድስት-አኃዝ ፒን-ቁጥርዎን በማስገባት አዲሱን አገልግሎት መጠቀም ይችላሉ።

ይህንን በማድረግ የኦንላይን ግብይቶች ለመፈጸም፣ እንዲሁም ኢንሹራንሶች፣ ባንኮች፣ የኢሜይል አገልግሎት-ሰጭ ድርጅቶች፣ የተለያዩ የኢንተርኔት ማህበራዊ ግንኙነት ድረ-ገፆች የሚሰጡትን አገልግሎቶች ማግኘት ይችላሉ። የመንግሥት ባለስልጣን መ/ቤቶችም ቢሆኑ የእዚህን ዓይነት የኦንላይን አገልግሎት አቅርቦቶቻቸውን ወደፊት እያስፋፉ እንደሚሄዱ ይታመናል። eATዎን በመጠቀም በኦንላይን ተሽከርካሪ መኪና ኢንሹራንስ ማስገባትና በሚመለከተው የመንግሥት መ/ቤት የማስመዝገብ ተግባር በቀላሉ ማከናወን ይችላሉ። ትዕግስት አስጨራሽ የሆኑ የኢንተርኔት ፎርሞችን በመሙላት ወይም ጉዳይዎን ለማስፈጸም ወደ መንግሥት መ/ቤት በመሄድና ወረፋ በመጠበቅ እንዲሁም ተቀምጠው ፎርሞችን በመሙላት የሚያጠፉት ጊዜ ይወገዳል።

## አዲሱን በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴ መጠቀም የሚችለው ማን ነው?

አዲሱን የኦንላይን ማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት መጠቀም የሚችሉት ዕድሜያቸው 16 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው። ይሁንና ይህን አገልግሎት የመጠቀም አለመጠቀም መብቱ የእርስዎ ነው። ፍላጎትዎ ከሆነ በፈለጉበት ጊዜ አገልግሎቱን መጠቀም ከመቻልዎም በላይ ሃሳብዎን ከለወጡም ደግሞ እንዲቋረጥ ማድረግ ይቻላል።

## በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴ መጠቀም የሚቻለው እንዴት ነው?

በeAT የእርስዎን ማንነት ለማረጋገጥ ይችሉ ዘንድ የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴው ሁልግዜም ለአገልግሎት ክፍት ሆኖ መገኘት አለበት።

የካርድ ማንበብያ መሳሪያና ድራይቨር ሶፍትዌር፣

- የኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ eAT ካርድዎን ከኮምፒውተርዎ ጋር ለመጠቀም ከፈለጉ የካርድ ማንበቢያ መሳሪያ (ተስማሚ መሳሪያ በኮምፒውተር ሱቆች ይገኛል) እና
- eAT ካርድና ኮምፒዩተሩ እንዲናበቡ „AusweisApp“ የተባለ ድራይቨር ሶፍትዌር ያስፈልግዎታል። ይህን ሶፍትዌር ከwww.ausweisapp.bund.de ድረ-ገፅ ወስደው ኮምፒውተርዎ ላይ መጫን ይችላሉ።



የግል መለያ ምስጢራዊ ቁጥር ደብዳቤ (ፒን-ደብዳቤ)

የኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ eAT ካርድ እንዲሰጥዎት ካመለከቱ በኋላ የፒን-ቁጥር ደብዳቤ የተባለው በፖስታ አማካይነት ይላክልዎታል። በፒን-ደብዳቤው አማካይነት ባለ5-አሃዝ የግል መለያ ቁጥር፣ ባለ10-አሃዝ የፒን መክፈቻ ቁልፍ (PUK) እና እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የኦንላይን ማንነት ማረጋገጫ አገልግሎትን ለማገድ የሚያስችል ሚስጢራዊ የየኮድ-ቃል ይላክልዎታል።

የግል መለያ ምስጢራዊ ቁጥር (ፒን-ቁጥር)

**ልብ ይበሉ፣**
ይህ የሚላክልዎት ባለ 5-አሃዝ የፒን-ቁጥር በጊዜያዊነት (Transport-PIN ተብሎ ይታወቃል) የሚሰጥዎ በመሆኑ eAT ካርድ ከተቀበሉ በኂላ እራስዎ በመረጡት በሌላ ባለ 6 አሃዝ የፒን-ቁጥር መተካት አለበት።

የፒን-ቁጥሩን እቤትዎ ባለው የካርድ ማንበቢያ መሳሪያ ራስዎ መለወጥ ወይም የእርስዎን ጉዳይ በሚከታተለው የውጭ ዜጎች ጉዳይ መ/ቤት አማካይነት ማስለወጥ ይችላሉ። ፒኑን ካለምንም ገደብ በፈለጉበት ጊዜ በሌላ አዲስ ፒን መለወጥ ይችላሉ። ሁል ጊዜም በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ሲጠቀሙ ባለ6-አሃዝ የፒን-ቁጥርዎን መጠቀም አለብዎት።

የግል መለያ ምስጢራዊ ቁጥር (ፒን-ቁጥር) መክፈቻ ቁልፍ (PUK)፣
ሶስት ጊዜ በተከታታይ የተሳሳተ ፒን ከተጠቀሙ ካርድዎ የሚሰጠውን አገልግሎት ያቋርጣል። የፒን መክፈቻ ቁልፉ (PUK) የተዘጋውን የፒን-ቁጥር አገልግሎት መልሶ ለመክፈት ያገለግላል።

አገልግሎት ለማቋረጥ የሚያስችል ሚስጢራዊ የኮድ-ቃል፣
የኤሌክትሮኒክ የመኖሪያ ፈቃድ የኮድ-ቃል eAT ካርድዎ ቢጠፋ ወይም ቢሰረቅ አገልግሎቱን ወዲያው በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት አማካይነት ማዘጋት አለብዎት። ይህንንም ለማድረግ የሚችሉት ለዚህ ጉዳይ ተብሎ በተዘጋጀው የስልክ መስመር ደዉሎ በመንገር ወይም የእርስዎን ጉዳይ ወደ ሚከታተለው የውጭ ዜጎች ጉዳይ መ/ቤት በመሄድ አገልግሎቱን ለማሳገድ የሚያስችለውን ሚስጢራዊ የኮድ-ቃል በመንገር ይሆናል።

**ለግል መረጃ የሚደረግ ጥበቃ**
የፒን-ቁጥሩን፣ የፒን መክፈቻ ቁልፉን (PUK) እና አገልግሎቱን ለማሳገድ የሚያስችለውን የኮድ-ቃል በeAT ካርድዎ ላይ እንዳይጽፉ ይጠንቀቁ።

## ማስመሰያ ስም (Pseudonym) ምንድን ነው?

የግል ማንነት ማረጋገጫ መረጃዎን ሳይገልፁ eAT ካርድዎን በመጠቀም፣ ለምሳሌ በማህበራዊ ግንኙነት ድረ-ገፆች ራስዎን ማስተዋወቅ ይችላሉ። ለእዚህ ተግባር eAT ካርድ ውስጥ ያለው ችፕ የእርስዎን ማንነት የሚመለከቱ የግል መረጃዎችዎ ሳይገለጹ ከአገልግሎት-ሰጭው ድረ-ገፅ ጋር ለማገናኘት የሚያስችል ማስመሰያ ስም በመፍጠር እንደ ተጠቃሚ ያስተዋውቅዎታል። የስድስት-አሃዝ ፒን-ቁጥር አጠቃቀም እንደ ተለመደው የሎግ ኢን (log-in) አሠራር ሂደቱ በጣም ቀላል ከመሆኑም ባሻገር ለአደጋ የመጋለጡ ዕድል ግን በጣም ዝቅተኛ ነው።

## ዕድሜንና የመኖሪያ ቦታን ማጣራት ምንን ያመለክታል?

አንዳንድ የኦንላይን አገልገሎት-ሰጪዎች የተጠቃሚውን ግለሰብ ዕድሜና መኖሪያ አድራሻ ማጣራት ይፈልጋሉ። ለእዚህም eAT የዕድሜ ወይም የመኖሪያ አድራሻን ትክክለኛነት የማጣራት ተግባር ያከናውናል። ዕድሜን በተመለከተ eAT ሙሉ የትውልድ ቀን ወርና ዓ.ም. በማሳወቅ ፈንታ የሚያስተላልፈው መረጃ የeATው ካርድ ባለቤት ተፈላጊው ዕድሜ (ለምሳሌ 16 ዓመት) የሞላው መሆኑን ብቻ ነው።

የመኖሪያ አድራሻን ትክክለኛነት ማጣራትን በተመለከተ ግለሰቡ በሰጠው የመኖሪያ አድራሻ አካባቢ ወይም ክልል ውስጥ በእርግጥ በነዋሪነት የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

ይህም የመረጃ ስብስብን ለመቀነስና እንዲሁም ለአገልግሎት ሰጭው የሚተላለፉት መረጃ ዎች ሁሉ ለሚፈለገው አገልግሎት የግድ አስፈላጊ ናቸው የተባሉት ብቻ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡

## በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴ ስለመጠቀም፣ ለምሳሌ በኦንላይን ግብይት ማካሄድ



መጀመሪያ ከኦንላይን ነጋዴው የሚገዙትን ዕቃ ይመርጣሉ፡፡ ነጋዴውም የግብይቱን ውል ስምምነት ለማጠናቀቅና ከደረሰኙ ጋር ዕቃውን መላክ ይችል ዘንድ ሙሉ ስምዎንና አድራሻዎን ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ይህን መረጃ በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ቴክኒክ ለነጋዴው ሊያስተላልፉ ይችላሉ፡፡



መረጃው ከመተላለፉ በፊት የኦንላይን ነጋዴው ለእርስዎ eAT ራሱን በፈቃድ ሰርቲፊኬቱ አማካይነት ያስተዋውቃል፡፡ የእርስዎ eAT ደግሞ የነጋዴውን የማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ትክክለኛነት መርምሮ ያረጋግጣል፡፡ ነጋዴው ደግሞ በበኩሉ በራሱ ሲስተም የእርስዎ eAT ሕጋዊ ተቀባይነት ያለውና ያልታገደ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡



የትኛዎቹን መረጃዎች ማስተላለፍ እንደሚፈልጉ ወይም እንደማይፈልጉ በሚከፈተው የኦንላይን የመምረጫ መስኮት ውስጥ ፈልገው ምልክት ያደርጋሉ፡፡ ከእዚያም የእርስዎን ባለ6-አሃዝ ፒን-ቁጥር ካስገቡ መረጃው ወደ ነጋዴው እንዲተላለፍ ተስማምተዋል ማለት ነው፡፡ የመረጃ ማስተላለፍ ተግባር በሚስጥራዊ-ኮድ አማካይነት ነው የሚጠናቀቀው፡፡

የግዥ ፈቃደኛነትዎን የሚገልጽ ራሱን የቻለ የተለየ ማረጋገጫ ሲሰጡ የውል ስምምነቱ ተፈፃሚ ሆነ ማለት ነው፡፡

!

**ልብ ይብሉ፣**

አሁን አዲሱን የመኖሪያ ፈቃድዎን በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ሄደው ሲቀበሉ፣ የኦንላይን ማንነት ማረጋገጫውን መጠቀም ይፈልጋሉ? አይፈልጉም? ተብለው ይጠየቃሉ፡፡ በእርስዎ ውሳኔ መሠረት የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫዉ ለአገልግሎት ክፍት ወይም ዝግ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የሆነ ሆኖ በማንኛውም ጊዜ ሃሳብዎን ቢለውጡ በውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለስልጣን መ/ቤት አማካይነት የኦንላይን ማንነት ማረጋገጫ ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆንልዎ ወይም እንዲዘጋ ማስደረግ ይችላሉ፡፡

# 5 የኤሌክትሮኒክ ፊርማ፣

የeAT ካርድዎ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ማስፈር እንዲያስችል ተቀባይነት ያለው ኤሌክትሮኒክ ፊርማ Qualified Electronic Signatures (QES) በተባለው የአሠራር ቴክኒክ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀ ነው። ሆኖም የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ለመጠቀም ይችሉ ዘንድ አገልገሎቱን መክፈት/አክቲቬት ማድረግ የሚችሉት እስዎ ብቻ ነዎት።



## የኤሌክትሮኒክ ፊርማ አሠራር እንዴት ነው?

ለምሳሌ በዲጂታል መልክ የቀረበ የውል ስምምነት ሰነድ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ከሰፈረበት በኋላ ሕጋዊ ተፈፃሚነት ይኖረዋል። ይህም ሊሆን የቻለው መደበኛውና በሰፊው የሚሠራበት የእጅ ፊርማ፣ የፊርማ ሰርቲፊኬት (Signaturzertifikat) ተብሎ በሚታወቀው ዘዴ በመተካቱ ነው። ሰነዱ ሁለቱም ወገኖች ተስማምተውበት የዲጂታል ፊርማ ከሰፈረበት በኋላ ለውጥ ተደርጎበት ከሆነ፣ የሰነዱ ተቀባይ (የውል ተቀባዩ) በኤሌክትሮኒክ ፊርማው አማካይነት ለዉጡን እንዲያውቅ ይደረጋል።

eAT የዲጂታል ፊርማ በሰነዶች ላይ ማስፈር እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ ካርድ ነው። የዲጂታል ፊርማ በሰነዶች ላይ ማስፈር እንዲቻል የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴው ለአገልግሎት ክፍት መሆን ይኖርበታል።



## የፊርማ አገልግሎቱን መጠቀም እንድችል ምን ያስፈልገኛል?

ማንኛዉም የeAT ካርድ ባለቤት የፊርማ አገልግሎቱን መጠቀም የሚችለው በራሱ ፍላጎት ብቻ ነው። አገልግሎቱን ለመጠቀምም የተለየና ለእዚሁ ተግባር የሚያገለግል የፊርማ ሰርቲፊኬትና በእጅ ሊያዝ የሚችል የካርድ ማንበቢያ መሳሪያ መግዛት ይኖርብዎታል። የመሳሪያውም ዋጋ ከቦታ ቦታ ይለያያል።

የፊርማ ሰርቲፊኬት (Signaturzertifikat)

የፊርማ ሰርቲፊኬት ሕጋዊ ፈቃድ ከተሰጠው የፊርማ አገልግሎት-ሰጪ ድርጅት Zertifizierungsdiensteanbieter ተብሎ ከሚጠራው መግዛት ይቻላል። የእነዚህን አገልግሎት-ሰጭ ድርጅቶች ስም ዝርዝር ከፌዴራል ኔትዎርክ ኤጀንሲ ድረ-ገፅ (www.nrca-ds.de/en/index_e.html) ውስጥ „Akkreditierte ZDA“ በሚለው ርዕስ ስር ማግኘት ይችላሉ። አገልግሎቱን ለመጠቀም የፊርማ ሰርቲፍኬት ሶፍትዌርን በeAT ካርድዎ ላይ መጫን ይኖርብዎታል።

የፊርማ-ፒን (Signatur-PIN)፣

የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ለመጠቀም ራሱን የቻለ ለእዚሁ ተግባር ተብሎ የተዘጋጀ የፊርማ-ፒን ያስፈልግዎታል። የፊርማ ሰርቲፊኬት ሶፍትዌር ካርድዎ ላይ እንደገና ሲጭኑ ፒኑን ራስዎ መሙላት ይኖርብዎታል።

በእጅ ሊያዝ የሚችል የካርድ ማንበቢያ መሳሪያ፣

የቁጥር-ኮድ ሊያሳይ የሚችልና (Display) ንክኪ የማይፈልጉ ግንኙነቶችን ሊቀበልና በእጅ ሊያዝ የሚችል የካርድ ማንበቢያ መሳሪያ (PIN-Pad) ያስፈልግዎታል። የሶፍትዌሩን አጠቃቀም በተመለከተ መመሪያውን ይመልከቱ።



# 6 የመኖሪያ ፈቃድ ካርድዎ ሊያሰጥዎት የሚችለው አዳዲስ ጠቃሚ አገልግሎቶች




**በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴ አገልግሎቶች፣**
የኦንላይን-ምዝገባ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንድ የኦንላይን አገልግሎት-ሰጭ ድርጅት ሲመዘገቡ የተለያዩ የእርስዎን ማንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን እንዲሰጡ ይጠየቃሉ። የሚጠየቁትም ስምዎን እንዲሁም እንደየሁኔታው ሙሉ አድራሻዎን ሊሆን ይችላል። እነዚህን መረጃዎች በeAT ካርድዎ አማካይነት በቀላሉ በማስተላለፍ የእስዎን ማንነት ማረጋገጥ ይችላሉ።




ማሽኖችን በመጠቀም የእስዎን ማንነት ማረጋገጥ ስለመቻል፣ የእጅ በእጅ መሸጭያ ማሽ ኖች እንዲሁም የመረጃ-ሰጭ መሳሪያዎች የሚሰጡት አገልግሎት ወደፊት ይበልጥ እየተስፋፋ እንደሚሄድ ይታመናል። በእዚህም ለመጠቀም በeAT ካርድዎ አማካይነት የእስዎን ማንነት ማረጋገጥ ይችላሉ።




ለኢንተርኔት አገልግሎት የማስመሰያ ሽፋን ስም (Pseudonym) ስለመጠቀም፣ በማንኛውም ግዜ በኢንተርኔት ሲጠቀሙ የግልዎን ማንነት የሚመለከቱ መረጃዎች መስጠት የለብዎትም። ሆኖም የኦንላይን አገልግሎት ሰጪዎች ከእዚህ በፊት የተመዘገቡ ደንበኞቻቸውን መልሰው „ማስታወስ" የሚፈልጉበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል። ለእዚህ ም ተግባር የeAT ካርድዎ የማስመሰያ ስም ይፈጥራል።




የኦንላይን ፊርማ፣ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ በመጠቀም በኦንላይን የሚደረጉ ሕጋዊ ተፈጻሚነት ያላቸው የተለያዩ የውል ስምምነቶች ቀላልና ምቹ በሆነ መልኩ ማከናወን ይችላሉ።




የዕድሜ ወይም የመኖሪያ አድራሻ ትክክለኛነት ማረጋገጫ፣ አንዳንድ የኦንላይን አገልግሎቶችን መጠቀም የሚፈቀደው ተጠቃሚው ግለሰብ የተወሰነ የዕድሜ እርከን ላይ የደረሰ፣ ወይም በአንድ በተወሰነ አካባቢ በነዋሪነት የተመዘገበ እንደሆነ ብቻ ነው። የeAT ካርድ የግለሰቡን ዕድሜና የመኖሪያ አከባቢ ሊያረጋግጥ ይችላል። እዚህ ላይ ካርዱ የሚያስተላልፈው መረጃ „አዎ" ወይም „አይደለም" („Ja" ወይም „Nein") የሚል ይሆናል።




የኤሌክተሮኒክ ቅፅ ስለመሙላት፣ የኦንላይን ቅፃችን መሙላት በአብዛኛው ትዕግስት አስጨራሽ ነው። ስምና አድራሻ ሲጻፍ የሥርዓተ ሆሄያት ግድፈት በቀላሉ ሊከሰት ይችላል። መረጃው ቀጥታ ከeAT በኤሌክትሮኒክ መልክ በኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት አማካይነት ይተላለፋል።

ከባለሥልጣን መ/ቤቶች ጋር ሊኖር ስለሚችል ግኑኝነት፣ ወደፊት የአገልግሎት አቅርቦታቸውን (ለምሳሌ የኤሌክትሮኒክ ታክስ ገቢ ቅፅ በኦንላይን መላክ/ማስተላለፍ) ይበልጥ በኢንተርኔት መድረክ የሚያደርጉ የባለሥልጣን መ/ቤቶች ቁጥራቸው እየጨመረ እንደሚሄድ ይታመናል። ለእንደዚህ ዓይነት አገልግሎቶች የተጠቃሚውን ግለሰብ ማንነት አስመልክቶ አስተማማኝ መረጃ እንዲኖር ያስፈልጋል። ስለሆነም ወደፊት የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ አገልግሎት ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

# 7 የመረጃ ደህንነት አያያዝና ጥበቃ (Datensicherheit)

## የትኞዎቹ መረጃዎች ናቸው በeAT አማካይነት የሚተላለፉት?

የፒን-ቁጥር በማስገባት የሚከተሉትን መረጃዎች ማስተላለፍ ይቻላል፣

- ስም እና የወላጅ ስም; እንደአስፈላጊነቱ የትምህርት ደረጃ
- የሰጠው አገር
- የዕድሜና የመኖሪያ አካባቢ ትክክለኛነት ማረጋገጫ
- የትውልድ ቦታና ቀን
- የመኖሪያ አድራሻ
- የሰነድ ዓይነት
- በማስመሰያው ስም ላይ የተመሠረተ የማንነት ማረጋገጫ

## የትኛው መረጃ ለሌላው አካል እንደሚተላለፍ የመወሰን መብቱ የእርስዎ ነው፤

የeAT ካርድ ባለቤት እንደመሆንዎ የትኛው እርስዎን የሚመለከት መረጃ በኦንላይን ሊተላለፍ እንደሚችል የሚወስኑት እርስዎ ብቻ ነዎት። ከእርስዎ ፈቃድ ውጭ የሚተላለፍ መረጃ ቢኖር ግን የያዙት የeAT ካርድ ሕጋዊ ተቀባይነት አለው ወይም ታግዷል የሚለው መረጃ ብቻ ነው። የeAT ካርድዎ ታግዶ መሆኑንና አለመሆኑን ማወቅ ይችላሉ።

## እኔን በግል የሚመለከቱ መረጃዎች አስተማማኝ ጥበቃ ይደረግላቸዋል?

አዎን! ይልቁንም eAT ካርድዎን ሳይጠቀሙ ኢንተርኔት ውስጥ በሚንቀሳቀሱበት ወቅት፣ ለዕቃ ግብይትም ሆነሌላ የማህበራዊ ግንኙነት ድረ-ገፆችን በሚጎበኙበት ወቅት ለአደጋ የመጋለጥዎ ዕድል ከፍ ያለ ነው። ስለዚህም አዲሱ ካርድዎ በተሰጠው ተጨማሪ ተግባር መሠረት የግልዎ መረጃዎች ደህንነት የተጠበቀ ነው። ከአንድ የኦንላይን አገልግሎት-ሰጭ ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት የአገልግሎት-ሰጭውን ማንነት በእርግጥ የሚፈልጉት አካል ለመሆኑ የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ዘዴው ያጣራልዎታል።።

## መረጃዎቹ በሚተላለፉበት ወቅት በጠላፊዎች (Hacker) የማደናቀፍ አደጋ ሊከሰት ይችላል?

የመረጃ ማስተላለፍ ተግባር የሚከናወነው በሚስጥራዊ-ኮድ አማካይነት ነው። ሁሉም መረጃዎች የሚተላለፉት ዓለም አቀፋዊ እውቅናና ተሞክሮ ባለው አስተማማኝ የሚስጥራዊ-ኮድ ዘዴ ነው። eATን ለንግድ ሥራ መጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም አገልግሎት-ሰጭ ድርጅት ወይም ግለሰብ ከመንግሥታዊ ባለሥልጣን መ/ቤት (Vergabestelle für Berechtigungszertifikate/VfB) የፈርማ ፈቃድ ሰርቴፊኬት ማግኘት ይኖርበታል። ይህንን የፊርማ ፈቃድ ሰርቴፊኬት የሚሰጠው ባለሥልጣን መ/ቤት በበኩሉ ጥብቅ መሥፈርቶች ላይ በመመርኮዝ አመልካች ሥራውን ያከናውን ዘንድ እጅግ ቢያንስ ምን መረጃዎች/ዳታዎች ያስፈልጉታል ብሎ ከወሰነ በኋላ ለእነዚህ መረጃዎች/ዳታዎች ብቻ የሚሆን የፈቃድ ሰርቴፊኬት ይሰጠዋል።

# 8 የመኖሪያ ፈቃድ ካርድዎ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ ምን ዓይነት ችግር ሊያጋጥምዎት ይችላል?




## eAT ቢሰረቅብኝ ወይም ቢጠፋብኝ የሚሰጠውን የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ሌላ አካል እንዳይጠቀምበት እንዴት ማሳገድ እችላለሁ?

በስልክ ቁጥር (Hotline) 0180-1-33 33 33 በመደወል eAT እንዲታገድ ማድረግ ይችላሉ፡፡ (ለዚህም በጀርመን መስመር ስልክ 3.9 ሣንቲም በደቂቃ ወይም በሞባይል 42 ሳንቲም በደቂቃ ሲሆን፣ ከውጭ ሀገር ሆኖም መደወል ይቻላል)፡፡ በእዚህ ስልክ ቁጥር ሲደውሉ ስምዎን፣ የትውልድ ቀንና eATን ለማገድ የሚያስችለውን የኮድ-ቃል እንዲናገሩ ይጠየቃሉ፡፡ ስለሆነም ማንም ሰው ከእስዎ ሌላ eATን ለማሳገድ አይችልም፡፡ ይህ ጉዳይ ለሚመለከተውና በተለይ የአስዎን ጉዳይ ለሚከታተለው የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት የeATውን መጥፋት በፍጥነት ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡ በአማራጭም ወደ ውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት በመሄድ የeATን መጥፋት ማሳወቅ ይችላሉ፡፡

## eAT ቢጠፋ የኤሌክትሮኒክ ፊርማን አስመልክቶ ምን ሊከሰት ይችላል?

eAT መጥፋቱን ወዲያውኑ ለፊርማ አገልግሎት-ሰጭው በማሳወቅ እንዲታገድ ማድረግ አለብዎት፡፡ የሰነድዎን መጥፋት ለውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት ማሳወቅዎ ብቻ በቂ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ወዲያውኑ በአፋጣኝ ለፊርማ አገልግሎት-ሰጭው ድርጅት ማሳወቅ ይኖርብዎታል፡፡

# 9 ሌሎች ችግሮች ሲያጋጥሙስ ምን ይደረጋል ...?

### ... የተሳሳተ የፒን-ቁጥር ባስገባ?

ሁለት ጊዜ የተሳሳተ የፒን-ቁጥር ያስገቡ እንደሆነ eAT ካርድ ፊት ገጽ ላይ የሚገኘውን የመግቢያ ቁጥር (Zugangsnummer) በጥንቃቄ እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። ሆኖም ለሦስተኛ ጊዜ የተሳሰተ የፒን-ቁጥር ቢያስገቡ የኦንላይን አገልግሎቱ ወዲያውኑ ይታገዳል። የታገደውን ካርድ በፒን-ቁጥር መክፍቻ ቁልፍ (PUK) መልሰው መክፈት ይችላሉ። የእዚህን ዓይነት ችግር ሲገጥምዎት የፒን-ቁጥር መፍቻ ቁልፉን (PUK) እስከ አስር ጊዜ ደጋግመው መጠቀም ይችላሉ።

### ... የፒን-ቁጥሬን ብረሳውስ?

የትኛውም የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት eATዎን ሲያቀርቡ አዲስ ፒን-ቁጥር ይሰጥዎታል።

### ... የመኖሪያ አድራሻዬን ብለውጥስ?

ለአዲሱ አድራሻዎ ቅርብ ወደ ሆነው ጉዳዩ የሚመለከተው መ/ቤት፣ (የውጭ ዜጎች ጉዳይ ተከታታይ መ/ቤት ወይም የቀበሌ መመዝገቢያ መ/ቤት) በመሄድ ቢያመለክቱ ያለምንም ችግር ቺፑ ውስጥና eAT ካርዱ ላይ ያለውን አድራሻ ለውጦ በአዲስ ተክቶ ይሰጥዎታል።

### ... የፓስፖርቴ የአገልግሎት ጊዜ ሲያበቃስ?

የፓስፖርትዎ የአገልግሎት ጊዜው ከማብቃቱ ቀደም ብለው እንዲራዘምልዎት ያመልክቱ። የወደፊት eATዎ ሊያገለግል የሚችለው የፓስፖርትዎ አገልግሎት እስከሚያበቃበት ጊዜ ብቻ ነው።

### ... ከተወሰነ ግዜ በኋላ የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫውን ለአገልግሎት ክፍት እንዲደረግ ወይም እንዲቋረጥ ብፈልግስ?

የeAT አገልገሎት ጊዜ እስካላበቃ ድረስ በፈለጉበት ጊዜ በውጭ ዜጎች ጉዳይ መ/ቤት አማካይነት የኦንላይን የማንነት ማረጋገጫ ለአገልግሎት ክፍት እንዲሆንልዎ ወይም እንዲቋረጥ ሊያስደርጉ ይችላሉ።

# 10 የእኛ መ/ቤት፣ ማለትም የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት ችግርዎን ለመፍታት ምን ጊዜም ዝግጁ ነው!

የመኖሪያ ፈቃድ ማግኘት የሚቻለው በአካባቢው ለሚገኘው የውጭ ዜጎች ጉዳይ ባለሥልጣን መ/ቤት በማመልከት ነው። የማመልከቻውን ሂደት አስመልክቶ ዝርዝር መረጃ ከመ/ቤቱ ማግኘት ይችላሉ።

! ከዚህም በተጨማሪ ስልክ በመደወልም ከመረጃ አገልግሎት ቢሮ ጋር ግንኙነት መፍጠር ይችላሉ። የአገልግሎት ቢሮው የሥራ ሰዓት፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ7:00 ሰዓት እስከ 20:00 ሰዓት ነው። በስልክ ቁጥር 0180-1-33 33 33 በመደወል ማነጋገር ይችላሉ (በጀርመን መስመር ስልክ 3.9 ሣንቲም በደቂቃ ወይም በሞባይል 42 ሳንቲም በደቂቃ ሲሆን፣ ከውጭ ሀገር ሆኖም መደወል ይቻላል)።

## -በኤንተርኔት መረጃ ስለማግኘት-

እንደዚሁም በኢንተርኔት አድራሻ፣ www.bamf.de/eaufenthaltstitel ጠቅላላ የመረጃዎች ስብስብ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም ይኖራሉ ተብለው ለሚገመቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች ቁልፍ ማብራሪያዎች በድረ-ገፁ ላይ ይገኛሉ። በተዛማጅ ርዕሶች ላይም ለምሳሌ ስለፊርማ አገልግሎት-ሰርቲፊኬት ሰጭዎች ወይም „AusweisApp“ የተባለውን ድራይቨር ሶፍትዌር እንዴት አድርገው ኮምፒውተርዎ ላይ መጫን እንደሚችሉ ድረ-ገፁ ላይ ማብራሪያ ይገኛሉ።

| ምህጻረ ቃላት | |
|---|---|
| eAT | የኤሌክትሮኒክ መኖሪያ ፈቃድ (elektronischer Aufenthaltstitel) |
| PIN | የግል መለያ ቁጥር (ፒን-ቁጥር) (Personal Identification Number) |
| PUK | የፒን መክፈቻ ቁልፍ (Personal Unblocking Key) |
| QES | ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው የኤሌክትሮኒክ ፊርማ (Qualified Electronic Signature) |
| VfB | የፊርማ-ፈቃድ ሰርቲፊኬት የሚሰጠው ባለስልጣን መ/ቤት (Vergabestelle für Berechtigungszertifikate) |

## የጽሑፍ ዝግጅት

አርታዒና አሳታሚ፤
የፌዴራል ማይግሬሽንና ስደተኞች መስሪያ ቤት፤ Referat 230
የፌዴራል የሀገር ውስጥ ሚኒስቴር፤ Referat M I 6 und
Referat IT 4

ቀን
ፌብሩዋር 2011

አታሚ፤
Bonifatius GmbH
33100 Paderborn

ንድፍ፤
የፌዴራል ማይግሬሽንና ስደተኞች መስሪያ ቤት / Bundesamt
für Migration und Flüchtlinge
Gertraude Wichtrey
Claudia Sundelin